
ቅፅ 5 ቁጥር 64 ታህሳስ 1997 ዓ.ም.

# ኢትኦጵ



“ኢትዮጵያ እንደ ጋለሞታ ቤት የፈለገ የሚገባባትና የሚወጣባት አትሆንም”

ዶ/ር በፍቃዱ ደግፌ
(የቀስተደመና ፓርቲ ም/ፕሬዘደንት)











የኮሜዲያን ድግስ

- የሰራዊቱ መኮንኖች አቤቱታ
- “የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ” (ዶ/ር ነገደ ጎበዜ)
- ምርጫ፡ ህብረቱ 394 ኢህአዴግ 3
- የጠጣ ዘመን......(ገሞራው)



«ይህ ጉዳይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ችግር ሳይሆን የአቶ መለስ ችግር ነው:: ልነግርህ የምሞክረው የኢትዮጵያ ህዝብ ዳር ድንበሩን አረጋግጧል:: በድርድር የሚሰጠው የለም:: ከሔሳ አንጻር አቶ መለስ ከገቡበት ማጥ ለመውጣት ይህን መስመር ሊከተሉ ይችሉ ይሆናል:: ግን ይህም የሚያዋጣ ቸው አይመስለኝም:: በእርግጥ ጉዳዩ መሰረታዊ ችግር አለበት:: በሌሳ በኩል ደግሞ ይህ ጉዳይ መሰረታዊ ችግር የሆነውን ያህል መሰረታዊ ችግርም የማይሆ ንበት ሁኔታ አለ:: ችግሩ መሰረታዊ የሚሆነው አንድ ጊዜ ውሳ ኔው ከተሰጠ ያለምንም ይግባኝ እቀበላለሁ ብለው ቃላቸውን ሠጥተዋል:: የተደረሰበትን ውሳኔ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ አልተቀበለውም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ያኔም ሆነ አሁን እያለ ያለው «እኔ የሚገባኝን አግኝቻለሁ:: በርስዎ በኩል ግን የኔን ሳይነኩ ሰጥተው የሚቀበሉት ካለ መንገዱን ወርቅ ያድርግልዎት ነው:: በአጥንቴና በደሜ ያስከበርኩትን ዳር ድንበሬን አታስደፍሩብኝም» ነው

***ዶ/ር በፈቃዱ ደግፌ***

........................................................................13



ዛሬ በተቃዋሚዎች ሰፈር በመጭው ምርጫ ጉዳይ የተከሰቱት ልዩነቶች ተሳትፎ ወይስ ቦይኮት በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ብቻ ከተወሰኑ ማንም ያሸንፍ ማን የትም የሚያደርሱ «ክርክሮች» አይደሉም:: ዋናው የክርክር ነጥብ መሆን ያለበት በኢህአዴግ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ስር እስካለን ድረስ የምርጫ ሂደት ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ ያለው ሚና እና ተልዕኮ ምንድን ነው? የሚ ለው ጥያቄ ነው::

***ዶ/ር ነገደ ጐበዜ***

........................................................................9

በስተኋላ መለስ ዜናዊ ይህ ጉዳይ በሪፖርት ሲደርሳቸው ያብዳሉ:: «ማነው የትግሬው የበላይነት አለ ከሚለው መደምደሚያ ላይ እንድትደርሱ ያደረጋችሁ?...» በማለት የሁሉንም ኮር አዛዦችና ክፍለ ጦር አዛዦች አዲስ አበባ አስጠርተው ያፋጥጧቸዋል:: በወቅቱም:- «በጄኔራሎችና በክፍለ ጦር አዛዦች ስብሰባ ላይ ከንፈ እያወያየን ሳለ፣ የኦሮሞና የአማራ ተ ወላጆች የሆኑት ጀኔራሎችና ኮሎኔሎችከ ተቃውሞ አንስተዋል:: ከንፈም «አዎ! ልክ፣ ነው የትግሬ የበላይነት» አለ በማለት መልስ ሰጥተዋቸዋል

........................................................................11



...ይህን ኢ-ሰብአዊ ጥፍጨፋ ለመቃወም በተደረገው ሙከራ ላይ ነው ቻይና ተቃውማ የቆመችው:: የሰሃራን ድንበራዊ ጠርዝ ወደታች ለመግፋት፣ ዛሬ ከምንጊዜውም የከፋ ትግል እየተካሄደ ነው:: በዚህ ትግል ላይ የቻይናውያን ድጋፍ ለአረቦች መሆኑ፣ የነሱን የጥቁር ሕዝብ ጥላቻ በገሃድ አረጋግጧል:: የሀገራችንም የዘረኞች መንግሥት (ወያኔ)፣ ከነዚህ የጥቁር ሕዝብ ጠላት ከሆኑት ቻይናውያን ጋር ማበር፣ የወያኔንም ፀረ-ጥቁር ሕዝብ አቋም ያንፀባርቃል::

***ኃይሉ ገ/ዮሃንስ (ገሞራው)***

........................................................................24

«...የተሰረቁብኝ ስራዎች ከመኖራቸውም በተጨማሪ አንድ ወቅት ላይ አድናቂህ ነኝ በማለት ፒያሳ መሀል ፎቶግራፎችን አስነስቶኝ አሜሪካን አገር ወስዶ በፖስተር መልክ ወደ አ.አበባ የላከልኝን የመሰለ ጨካኝ ነጋዴዎች ያሉበት አገር ነው ያለነው:: በጣም ይገርማል... እነዚህ ሰዎች የምንተዋቸው ይመስላቸዋል እንጂ አንድ ቀን የሙያ ማህበራችን እየተደራጀና እየተጠናከረ ሲሄድ ለፍርድ መቅረባቸው አይቀርም»

***ኮሜዲያን እስረስ በቀለ***

........................................................................29



# ማውጫ


## ማሕበራዊ

ትዳርዎን ከፍረስ ያድኑ
....................ገፅ 4

## የፖለቲካ መድረክ

የኢትኦጵ የምርጫ ውጤት
....................ገፅ 6

«የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ»

ሕገ-መንግስት፣ ምርጫና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ
....................ገፅ 9

የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት አደረጃጀትና ውስጣዊ ችግሮች
....................ገፅ 11

## ቃለምልልስ

«ኢትዮጵያ እንደ ጋለሞታ ቤት የፈለገ የሚገባባት፣ ያልፈለገ የሚወጣባት አትሆንም»
....................ገፅ 13

## ሠውነት

ዲግሪ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ሲሆን
....................ገፅ 17

ታኮ ጫማ የሚመረጥባቸው 3 ምክንያቶች
....................ገፅ 20

ኦፍራ ሃዛ
....................ገፅ 20

## ትናንትና

የመኢሶን መስራች ዶ/ር ኃይሌ ፊዳ ቃል
....................ገፅ 23

በጠባ ዓመት የተመሠረተ የብልጣ ብልጦች ወዳጅነት፣ የጠባ ዓመት ሲያልቅ ይደረመሳል!
....................ገፅ 24

## ዓለም አቀፍ

ሱሰኛው ነፍሰ ገዳይ
....................ገፅ 26

## ጥበባት

ጨዋታ ከ6 ኮሜዲያን ጋር
....................ገፅ 29

## መነፅር

«ገዢው ፓርቲ የሃገሪቱን ችግር መፍታት አቅቶታል»
....................ገፅ 33

«እኔ አብሬዎ አልተወዳደርሁም»
....................ገፅ 36

## መንገድ

«የመጨረሻ ሥራዬ ጥሩንባ ነፊነት ሆነ»
....................ገፅ 40



# «የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ»

# ሕገ-መንግስት፣ ምርጫና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ውስጥ በተለይም ከ1966ቱ አብዮት በኋላ ስማቸው ጉልቶ ከሚጠቀሱ ፖለቲከኞችና ምሁራን አንዱ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ ናቸው፤ የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መኢሶን/ መሪ የሆኑት ዶ/ር ነገደ ጎበዜ አሁንም የዚሁ ፓርቲ መሪ ሲሆኑ፣ በዋሽንግተን የተመሰረተው የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት አመራር አባልም ናቸው፤ በሙያቸው ሕግንና ስነ-መንግስትን /ፖለቲካ ሳይንስ/ ያጠኑት ዶ/ር ነገደ ጎበዜ በቅርቡ አንድ መፅሐፍ ለንባብ አብቅተዋል። 208 ገፅ ያለው ይህ መፅሐፍ «ሕገ-መንግስት፣ ምርጫና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ከትላንት ወዲያ እስከ ነገ» የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን፣ ተቃዋሚዎች ትግላቸው ሕገ-መንግስቱን እስከመቀየር የዘለቀ መሆን እንዳለበት ያሳስባል፤ በደርግና በኢሕአዴግ ሕገ- መንግስት መካከል ያለው መመሳሰል አንዳንድ ስፍራዎች ቃላት አንድነት ጭምር የሚገለፀ መሆኑን ያመለክታል። ከአፄ ኃ/ስላሴ ዘመነ-መንግስት ጀምሮ ያለውንም ሕገ-መንግስታዊ ሁኔታም ይፈትሻል።

ይህ የዶ/ር ነገደ ጎበዜ መፅሐፍ ሕገ- መንግስት ከንጉሱ እስከ ደርግ፣ የምርጫ ስርአት ሕገ-መንግስታዊ ሂደት፣ የኢህአዴግ ስታሊናዊና አደገኛ ሕገ-መንግስት፣ ለሰላምና ለዲሞክራሲ አደገኛ ሰነድ ምርጫና ዲሞክራታይዜሽን በኢህአዴግ ሕገ-መንግስታዊ ስርአት፣ የሕገ-መንግስትና የምርጫ አልባነት ታሪክ በሚሉት ርዕሶች ላይ ፍተሻ አድርጓል። በቅርቡ ለንባብ የበቃውና እዚህ ሀገር ለሽያጭ ያልቀረበው የዶ/ር ነገደ ጎበዜ መፅሐፍ በመቅድሙ የሰፈረውንና ወቅታዊ የምርጫ ሁኔታን የሚቃኘውን አቅርበነዋል። ከዚያ ቀደም ብሎ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ በመፅሄፉ የጀርባ ሽፋን ላይ ያሰፈሩት መልዕክት እንመልከት፡-

## ዶ/ር ነገደ ጎበዜ

የኢሕአዴግን ሕገ-መንግስታዊ ስርአት በሰላማዊና ሕዝባዊ የትግል ማዕበል አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ዘመን መክፈት ምርጫ አይደለም። ሀገራዊ፣ ሰብአዊና የሞራል ግዴታ ነው። በዚህ በተቆላለፈ ሁኔታ ይህንን ኃላፊነት መወጣት አስቸጋሪ ይሆናል እንጂ የማይቻል አይደለም። ለዚህ ግን ከሁሉ አስቀድመን ትግላችን ከኢሕአዴግ ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሳችንም ጋር እንደሆነ መገንዘብ አለብን። ምርጫው ዓለም አቀፋዊ መስፈርቶችን ባሟላ ሁኔታ እንዲካሄድ ወያኔን ለማስገደድ የሚደረገው የፖለቲካና ዲፕሎማቲክ ጥረት የዚህ ትግል አንድ ዘርፍ ብቻ ነው። ለመጭው ትግልና ለማይቀረው ድል ከዚህ ይበልጥ ወሳኝ የሚሆነው ከወያኔ የማንጠይቀውና እሱም ሊከለክለን የማይቻለው እኛ ራሳችንም የቤት ስራችንን የመስራቱ ጉዳይ ነው።

ኢሕአዴግ ተከፋፍለን ብንፋለመው ይመርጣል።በአንድነት መቆማችንን ግን ባይፈቅደውም ሊከለክለን አይችልም። ኢሕአዴግ እኛ እንደምንፈልገው ዓለም አቀፋዊ የነጻ ምርጫ መስፈርቶችን ሙሉ በሙሉ ማሟላት ሊቸግረው ይችላል። እኛ ራሳችን የራሳችንን ቅድመ ሁኔታ ማሟላታችን ላይ ማተኮርን ግን ሊከለክለን አይችልም። ኢሕአዴግ የምርጫ ተሳትፏችን ፍሬ ቢስና በሻማ ያኸርነት መልክ እንዲሆን ቦይኮት ብናደርግ ደግሞ ይህ እርምጃ በትግል ላይ ያኮረፍን በሚያስመስለን መልክ ቢሆንለት ሰርግና ምላሽ ነው። ግን ደግሞ የተሳትፎም ሆነ የቦይኮት የትግል ስልታችን ለዴሞክራሲ የሚደረገውን ተጋድሎ በማያግዝ መልክ እናድርገው ብንል ይህንን ሊከለክለን አይችልም።

ትግላችን በየአምስት ዓመቱ የሚያገረሽ ፈዛዛ የምርጫ ሰሞን የተቃውሞ ግርግር እንዲሆንለት ይፈልጋል። ተአማኒነት ያለው አማራጭ አንግቦ ቀጣይነት ያለው ህያው የሕዝብ ትግል ማዕበል መቀስቀስ ደግሞ ኢሕአዴግ ሊከለክለን የማይቻለው የኛ የራሳችን የቤት ስራ ነው። እንግዲህ ይህንን ሁሉ ኃላፊነታችንን ለመወጣት እንዴት እንንቀሳቀስ?

### «የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ»

ለሀገራችን ነጻነት የሚደረገው ተጋድሎ ዘላለሙን «ምርጫ ሰሞን ግርግር» እንዲሆን እርግማን ያለብን ይመስል አምስት ዓመት ጠብቆ የተቃዋሚዎች ትግል እንደገና «እየተሟሟቀ» ነው። መከረኛው ሕዝባችን «ተባበሩ ወይ ተሰባበሩ» እያለ የሚደጋግመውን እሮሮ ላለመስማት አውቀን የተኛን ይመስል ትግሉ «በመሟሟቅ» ላይ ያለው «በኛና በነሱ» መሃል ሳይሆን




ጭራሹን በተቃዋሚዎች መሃከል እየሆነ መምጣቱን በመታዘብ ላይ ነን። በሀገር ፍቅራቸው በምንም የማይተናነሱና በፖለቲካ ትንተና በመጣ ነገር «የዝንብ ጠንጋራ ይለያሉ» ብለን የገመትናቸው በርካታ ወገኖቻችን ወያኔ ወጥመድ ውስጥ ዘው ብለው በመግባት ቁም ነገር ላይ ሳይሆን ፍሬ ከርስኪ ላይ አንድ በማያደርገን ሀገር ጉዳይና የሕብረት ትግል ላይ ከማተኮር ይልቅ በጠባብ ድርጅታዊ አጀንዳ እየተራኮቱ ለኢሕአዴግ «በምቹ» ተቃዋሚነት እየተሰለፉ ሲሄዱ እናያቸዋለን። በዚህ ላይ ደግሞ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የሀገራችን ዴሞክራቶችና አገር ወዳድ ኃይሎች ባለሙሉ ኃይላቸው ተቀናጅተው ትግሉ ውስጥ ገብተው ከፋፋዩን ለማውገዝና «ሀገሬና ሕዝቤ ይቅደሙ» የሚለውን ለማገገዝ ከመሰለፍ ይልቅ ተስፋ እየቆረጠ ከትግሉ መድረክ ራሳቸውን የማግለል አዝማሚያ እያሳዩ ነው። ይህ ሁኔታ ከቀጠለ የሀገራችንና የሕዝባችን እጣ ፈንታ «የሚሸሹበት ምሽግ ሲሸሽ ታየ» የሚባለው አይነት እንዳይሆን ስጋት አለን።

ዛሬ በተቃዋሚዎች ሰፈር በመጭው ምርጫ ጉዳይ የተከሰቱት ልዩነቶች ተሳትፎ ወይስ ቦይኮት በሚሉት ጥያቄዎች ዙሪያ ብቻ ከተወሰኑ ማንንም ያሸንፍ ማን የትም የሚያደርሱ «ክርክሮች» አይደሉም። ዋናው የክርክር ነጥብ መሆን ያለበት በኢህአዴግ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ስር እስካለን ድረስ የምርጫ ሂደት ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ውስጥ ያለው ሚናና ተልዕኮ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ነው። ይህንን በትክክል መልሰን የምርጫም ሆነ የሌሎች ህዝባዊና ሰላማዊ ትግሎች ተልዕኮ ዛሬ በሀገራችን የተተከለውን ስታሊናዊ ህገ-መንግታዊ ትግሎች ተልዕኮ ዛሬ በሀገራችን የተተከለውን ስታሊናዊ ህገ-መንግስት ቀይረን ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት ለማምጣት ነው ካልን ለምንና እንዴት እንደምንሳተፍ ወይም ቦይኮት እንደምናደርግ ግልፅና ህዝባዊ ስትራቴጂ ይኖረናል።

በኛ ግምት የዚህ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት መቀየር ጉዳዩ ሀገራዊ የጋራ አጀንዳ ነው። እንደ አልባሌ ጉዳይ ከቆጠርነው ህብረተሰቡንም ሆነ ዓለም አቀፍ ኮሙኒቲን የምናንቀሳቅስበት የጋራ ስትራቴጂ አይኖረንም። በዚህ የትም አይደረስ።

ይህ አጀንዳ ተረስቶ ክርክሩ በተሳትፎና በቦይኮት ጥያቄ ላይ ብቻ ከሆነ ድህረ ግንቦቱ ሁኔታ ምን ይሆናል? «ተሳታፊዎቹ» የተቆረጠላቸውን መቀመጫ አግኝተውና በተቃዋሚነት ፓርላማው ውስጥ ተሰይመው በህዝብ ተረስተው «ትግሉን» ይቀጥላሉ። የቦይኮት ደጋፊዎችም እስከሚቀጥለው «መስፈርቶች በተሻለ የሚሟሉበት» ምርጫ ድረስ የሚባል➔

ጠፍቶ ትግሉን «በሌላ ዘዴ» ማለትም በአትርሱን መልክ በሚወጡ የተቃውሞ መግለጫዎች ይያያዙታል።

የሁለቱም አካሄድ በምርጫው ሂደት በመጠቀም በአገር አቀፍ ደረጃ ተአማኒነትና ቀጣይነት ያለው ህዝባዊ የትግል ማዕበል ለመቀስቀስ እንዴት እንደማይረዳና ይህንን አካሄድ ለመወሰጥ ከተደራጅም ካልተደራጁም ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በኩል ምን መደረግ እንዳለበት በዚች መጽሀፍ ውስጥ በሰፊው ለመተንተን እንሞክራለን። እዚህ ላይ ግን ዋናው የኛ የትግል መፈክር «ሁሉም ለዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ይንቀሳቀስ» የሚለው ጥሪ ሆኖ ሳለ ይህ የትግል መስክ «ባለቤት» ያጣበትን ምክንያትና ይህ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ እንጠቁም።

ቢያንስ ላለፉት አርባ ዓመታት በሀገራችን ዴሞክራሲና ፍትህ እንዲነግሱ ይህ ነው የማይባል መከራና መስዋዕትነት የተከፈለባቸው ሰላማዊም ሆኑ የትጥቅ ትግሎች ተካሂደዋል። እስከ ዛሬ ግን ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊት አገር አልሆነችም። ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ሲኖሩ እንደ አንድ መሰረታዊ ምክንያት ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው በነዚሁ ሁሉ የትግል ዘመናት የዴሞክራሲያዊ ህገ- መንግስት ጥያቄ ትግላችን «እንጀራ ልጅ» ሆኖ የሚገባውን ቁልፍና ግንባር ቀደም ቦታ ያለመያዙ ጉዳይ ነው። ባለፉት ሰባ ዓመታት የተፈራረቁብን ሦስት ህገ-መንግስታት የተደነገጉት ለሀገሪቱ «ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት እናምጣ» ብለው በታገሉና በዚህ ጥያቄ ተቀናቃኞቻቸውን ድል አድርገው በወጡ ኃይሎች አይደለም። ይህ ደግሞ ለምን እነዚህን ሰነዶች በሙሉ ለህዝባችን የዴሞክራሲና የፍትህ ህልም መልስ አልባና በገዢዎችም ሆነ በተገዢዎች ዓይን የተናቁ የአገዛዝና የለውጥ መሳሪያዎች እንዳደረጋቸው በዚህ ጥናት ውስጥ ለማስረዳት እንሞክራለን።

ዛሬም ይህ ቁልፍ የሆነው የዴሞክራሲያዊ ህገ መንግስት ጉዳይ ተገቢ ቦታውን አግኝቶ ህብረተሰባችንን ከዳር እስከ ዳር የምናንቀሳቅስበት ጥያቄ አልሆነም። ይህ እስካልሆነ ድረስ ደግሞ እስካሁን እንደታየው ሊደነገጉ የሚችሉት ህገ-መንግስታት የገዢዎችን የመግዛት መብትና የተገዢዎችን ለ«ህገ-መንግስታዊው ስርዓት» የመንበርከክ ግዴታ የሚያረጋግጡ ሰነዶች ይሆናሉ እንጂ በሀገራችን ለገዢዎችም ለተገዢዎችም እኩል የሚሰራ ህገ-መንግስት እውነት የሚሆንበት ምንም ተአምር አይኖርም።

ዛሬ የምንገኝበት የሀገራችንም ተጨባጭ ሁኔታ ሆነ የአለም አቀፍም አካባቢ ለዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስትና ለመድበለ ፓርቲ ስርዓት የተመቻቸ ነው። በዚህም የተነሳ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ በሀገራችን ገዥዎችም፣ ተቃዋሚዎችም ከዚያም አልፎ በአጠቃላይ ህብረተሰቡም ዴሞክራሲን በህግ የበላይነት የማያረጋግጥና በመድብለ ፓርቲ ምርጫ በተግባር የሚተረጉም ስርዓት አስፈላጊ መሆኑን ይቀበላሉ። ግን ደግሞ ይህንን ሁሉ እውን የሚያደርገው የዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ጉዳይ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶት ትግል የሚካሄድበት ጥያቄ አይደለም።

ኢህአዴግ የዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስትን ጉዳይ የማያነሳበት ምክንያት ግልጽ ነው። በዚህ ኃይል ልፋፋ መሰረት ይህ ጥያቄ እልባት ያገኘ ጉዳይ ነው። ደርግን ድል አድርጎ ስልጣን ከተቆጣጠረ ወዲህ «በሀገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ» በሀገራችን የተሟላ ዴሞክራሲን የሚያረጋግጥ ህገ-መንግስት ተደንግጓል። በዓለም አቀፉም ኮሙኒቲ አካባቢ ያለው አስተሳሰብ ከዚህ ተመሳሳይ ነው። በብዙ ባዕዳን እምነት ሰብአዊ መብቶችን፣ የፕሬስ ነጻነትና የመሳሰሉ ነጥቦችን በተመለከተ አንዳንድ «በአፈፃፀም» የሚከሰቱ ጉድለቶች ቢኖሩም ዛሬ በሀገሪቱ የተዋጣለት ዴሞክራሲያዊ ህገ- መንግስት አለ።

ልብ ብሎ ለሚመለከት ሰው ትንሽ ግራ የሚያጋባው በዚህ ጉዳይ በተቃዋሚው ጎራ ያለው አስተሳሰብ ከዚህ ብዙም የራቀ አለመሆኑ ነው። የተቃዋሚዎች ትግል ትኩረት ሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ እንዲከበሩ መሟገት፣ ነፃው ፕሬስ ሲታፈን ኢህአዴግን ማጋለጥ፣ ምርጫ ሲባል ይህ ሂደት ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን በተሟላበት ሁኔታ እንዲካሄድ መታገል እንጂ ለዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ተብሎና በዚህ ጉዳይ አተኩሮ የተደረገ ሰላማዊ ሰልፍም ሆነ ሌላ የተካሄደ ትግል እስካሁን እምብዛም አልተመዘገበም። ለምን?

ዛሬ ትግላችን ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት በሚል ሳይሆን የመንግስትን ፖሊሲዎችና ውሳኔዎች በመዋጋት ላይ ያተኮረ ቢሆን ከዚህ ጀርባ ያለው «አለመግባባት» በጣም ግልፅ ይመስለናል። በህብረተሰባችን ፊት የተደቀኑት ችግሮች ከህገ-መንግስቱ ሳይሆን ኢህአዴግ «የገዛ ህገ-መንግስቱን ካለማክበሩ» የሚመነጩ ናቸው ብለው የሚያስቡ ብዙ ወገኖቻችን አሉ። እነዚህ ወገኖቻችን ምናልባት በዚህ ሰነድ ውስጥ አንቀፅ 39 እና አንቀፅ 40 የሚፈጥሯቸው ችግሮች ባይኖሩ ኖሮ «ህገ-መንግስቱ እስከተከበረ ድረስ» ሰብአዊ መብቶችም፣ ነፃ ፕሬስም፣ የህግ የበላይነትም፣ የዳኝነት ነጻነትም ይረጋገጡ ነበር የሚል እምነት አላቸው። በመሆኑም ትግላቸው እስከዚህም ይህ ህገ-መንግስት እንዳለ ተቀይሮ በዴሞክራሲዊ ህገ-መንግስት እንዲተካ ሳይሆን ወያኔ «ለራሱ ህገ- መንግስት ተገዢ እንዲሆን» መሟገት ሆኖ እናገኘዋለን። በዚህ ሁኔታ የህገ-መንግስታዊ ስርዓት ለውጥ የሚለው መፈክር ባለቤት ማጣቱ የሚያስገርም አይደለም። በኛ በኩል በዚህ በበርካታ ተቃዋሚ ድርጅቶች ሳይቀር የሚያስተጋባ አስተሳሰብ ጨርሶ አንስማማም።

በንጉሱና በደርግ ዘመን እንደታየው በኢህአዴግም ህገ-መንግስት ለህዝባችን ስፍር ቁጥር የሌላቸው መብቶች ታውቀውለታል። የኢህአዴግ ህገ መንግስት እንዲያውም ከዚህም አልፎ በይፋ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌን የተቀበለ ሰነድ ነው። እነዚህ መብቶች አይከበሩም እንላለን። ግን ብዙ ሰው እንደሚያስበው ይህ የሆነው ወያኔ ህገ- መንግስቱን «በመጣሱ» አይደለም። የችግሩ ምንጭ እነዚህ መብቶች ኢህአዴግ እንደልቡ በሚተረጉማቸው በዚሁ በህገ-መንግስቱ ውስጥ በተተከሉ ሌሎች አንቀፆች ሲታገዱ በመቻላቸው ነው። ዛሬ በኢትዮጵያ መድበለ ፓርቲ ስርዓት የለም። ይህ የሆነው ህገ-መንግስቱ በተጨባጭ መድብለ ፓርቲ ስርዓት ስለማይፈቅድ ነው እንጂ ኢህአዴግ «በህገ ወጥነት» በመሰማራቱ አይደለም። የዳኝነት ነፃነት ብሎ የለፈፈ ህገ- መንግስት እያለን የዳኝነት ነፃነት ደብዛው ቢጠፋ እነ አቶ መለስ ህገ-መንግስቱን «በመጣሳቸው» አይደለም።

ይኸው ህገ-መንግስታቸው እዛው በዛው የዳኝነቱን ስራ በሙሉ ቁጥጥራቸው ስር እንዲያደርጉ ስለሚያስችላቸው ነው። ዛሬ በሀገራችን የህግ የበላይነት የሌለው ጉዳዩ በህገ-መንግስቱ አንቀፅ «ሳይያገለት» ቀርቶ አይደለም። ይህ የሆነው የህግ የበላይነትን በአሸበረቁ አንቀፆች የሚደነግገው ህገ-መንግስት ራሱ በሌሎች አንቀጾች ገዢዎችን ከህግም ከህገ-መንግስትም በላይ ሆነው እንዲገዙ ስለሚፈቅድላቸው ነው።

ዛሬ በሀገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ቁልፍ ጥያቄ የትግላችን የማዕዘን ድንጋይ አድርገን ህብረተሰባችንን ይዘን እንታገል ስንል በሁለት መሰረታዊ ምክንያት ነው። እስከዛሬ ያለው ልምድ አንድ ህብረተሰብ ከዳር ዳር ተንቀሳቅሶ በሀገሪቱ ያለውን የኃይል ሚዛን በማያወላዳ ሁኔታ ሳይቀይር የሚታወጁ ህገ መንግስታት የህዝብ የበላይነት የሚያረጋግጡ ሰነዶች ሆነው አያውቁም። ሁለተኛው ምክንያት እንደ ማስጠንቀቂያም ሆኖ የሚቀርብ ነው። በዚህ መጽሀፍ በዝርዝር እንደምናሳየው ይህ ፈላጭ ቆራጭነትን የሚያነግስ ህገ መንግስት ለኢህአዴግ ብቻ ሳይሆን ሀገራችንን ለማንም ስልጣን ለያዘ «አላፊ አግዳሚ» ኃይል አምባገነን አገዛዝ አመቻችቶ ያስቀመጠ ሰነድ ነው። ለዚህ ነው ዛሬ ትግላችን በነጻ ምርጫ ጥያቄ ላይ ብቻ ሳይሆን ከዚያው እኩልና እንዲያውም ከዚያም ይበልጥ «ለዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት» በሚለው ጥሪ ዙሪያም መሆን አለበት።

ይቺ ትንሽ መፅሀፍ የህገ-መንግስት ጥያቄ «የኤክስፐርቶች» ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በጠቅላላው ዴሞክራቶችን፣ አገር ወዳዶችንና ምሁራንን ሁሉ የሚመለከት ጥያቄ እንደሆነ ግንዛቤ አስጨብጣ በዚህ «በተናቀ» ጉዳይ ውይይት እንዲከፈት ካገዘች ግቧን መታለች ማለት ይሆናል። ከዚያም ታልፎ ደግሞ በውጭም በውስጥም ያሉ የሀገራችን ዴሞክራቶች በየመስላቸው እየተደራጁ በፖለቲካውም በዲፕሎማሲውም መስክ «ለዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስታዊ ስርዓት» በሚለው ጥሪ እስከ ግንቦት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ባሻገር ለሚቀጥለው ትግል ራሳቸውን ካዘጋጁ ጥረታችን ከምናልመው በላይ ተሳክቷል እንላለን።

በዚህ መጽሀፍ የተካተቱት መጣጥፎች በተለያዩ ወቅቶች በሰባትም በስምንትም ዓመታት ልዩነት የተሰናዱ ናቸው። በተለይ የደርግንና የኢህአዴግን ህገ መንግስታት የሚመለከቱት ጥናታዊ ጽሁፎች አንዳንድ ቦታ የመደጋገም ሁኔታ ይታይባቸዋል። ይህንን የመደጋገም ችግር «ሁለት ቢመስሉም የደርግና የኢህአዴግን ህገ-መንግስታት «ከአንድ ወንዝ የተቀዱ» በአንድ ፍልስፍና የተገነቡና በርካታ ቦታዎች ቃል በቃል የሚወራረሱ ስለሆኑ ምንም ማድረግ አልተቻለም ብለን ማስናበት ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም ሰነዶች ራሳቸውን ችለው የተሰናዱ በመሆናቸው አንዱ ላይ የተገለፀው ሌላው ላይ አይደገም ብለን ብናወጣው የሃሳቦች መሟላትና መከታተል ተዛብቶ መጣጥፎቹ ግልጽነት ይጎድላቸዋል ብለን ስለሰጋን እንዳለ ልናቀርባቸው መርጠናል። በዚህ ሳቢያ ችግር ከተፈጠረ አንባቢን ይቅርታ እየጠየቅን መልካም ንባብ ብቻ ሳይሆን መልካም ቀጣይ ክርክርና ውይይት እንመኝለታለን።■